## ከአድልዎ ነፃ የመሆን መግለጫ
## እና የአድልዎ አቤቱታ አቀራረብ ሂደት

ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች እኩል የትምህርት እድሎችን እና እኩል የሥራ ዕድሎችን ያቀርባል።እንዲሁም በጾታ፣በዘር፣በእምነት፣በቆዳ ቀለም፣በሃይማኖት፣በትውልድ ሃገር፣በብሔራዊ መነሻ፣በእድሜ፣በነርቭ ልዩነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣ጾታዊ መግለጫን ወይም ማንነትን ጨምሮ፣በእርግዝና፣በየጋብቻ ሁኔታ፣አካላዊ ገጽታ፣ማንኛውም የስሜት ህዋሳት፣የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት መኖር፣በክብር የተሰናበቱ የቀድሞ የጦር ኃይሎች አባል ወይም የወታደራዊ ደረጃ፣ቤት አልባነት፣ጎሳ፣የስደት ወይም የዜግነት ሁኔታ፣ወይም የሰለጠነ የመመሪያ ውሻ ወይም የአገልግሎት እንስሳ መጠቀምን መሰረት በማድረግ በማንኛውም ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴዎች አድልዎ አያደርግም።ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ለBoy Scouts of America እና ለሌሎች የወጣቶች ቡድኖችም እኩል ተደራሽነትን ያዘጋጃል።

### አድልዎ ምንድን ነው?

አድልዎ (Discrimination) ማለት አንድ ሰው ወይም የሰዎች ስብስብ በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት ማኅበረሰብ (protected class) አባል በመሆኑ/በመሆናቸው ምክንያት በእነሱ ላይ የሚፈጸም ሕገ-ወጥ አሠራር ወይም በደል ነው።አድልዎ አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ ከሚደረግለት ማኅበረሰብ (protected class) አባል በመሆኑ ምክንያት በተለየ መንገድ ማስተናገድ ወይም በአንድ ፕሮግራም፣አገልግሎት ወይም እንቅስቃሴ ውስጥ የመሳተፍ ዕድልን ወይም ተደራሽነትን መከልከል፣ወይም ለአንድ አካል ጉዳተኛ ሰው የሚያስፈልገውን ተገቢውን ሁኔታ (ማመቻቸት) አለማድረግ ሊያካትት ይችላል።አድሏዊ ትንኮሳ (Discriminatory harassment) የሚባለው ደግሞ አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ ከሚደረግለት ማኅበረሰብ አባል በመሆኑ ምክንያት ተመስርቶ የሚፈጸም የቃል (የንግግር) ወይም የአካል ትንኮሳ ነው።

### በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት ማኅበረሰብ(a protected class) ምንድን ነው?

በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት ማኅበረሰብ (Protected Class) ማለት በፌዴራል፣በክልል ወይም በአካባቢ ሕጎች ከአድልዎ እና ከትንኮሳ ጥበቃ የሚደረግላቸው፣የጋራ ባህሪያት ያላቸው የሰዎች ስብስብ ማለት ነው።በሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሕግ ጥበቃ የሚደረግላቸው ማኅበረሰቦች (Protected classes) የሚባሉት፣ከላይ በተጠቀሰው «ከአድልዎ ነፃ የመሆን መግለጫ» ውስጥ የተዘረዘሩት እንደ ጾታ፣ዘር እና የመሳሰሉት ቡድኖች ናቸው።

### ስለ የአድልዎ አቤቱታ እንዴት ማቅረብ እችላለሁ?

አንድ ሰው በትምህርት ቤት ወይም በሥራ አካባቢ አድልዎ ወይም አድሎአዊ ትንኮሳ ደርሶበታል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣መደበኛ ቅሬታ የማቅረብ መብት አለዎት።የትምህርት ዲስትሪክቱን የአድልዎ አቤቱታ አቀራረብ ሂደት ሙሉ ቅጂ ለማግኘት፣የተማሪዎች ሲቪል መብቶች ቢሮ (Office of Student Civil Rights)ድረ-ገጽ https://www.seattleschools.org/departments/student-civil-rights/ ይጎብኙ።

ቅሬታዎን ከማቅረብዎ በፊት፣ስጋቶችዎን ወይም ቅሬታዎን ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ-መምህር፣ከሥራ ቦታው ተቆጣጣሪ (supervisor)፣ወይም ከሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የእንባ ጠባቂ (Ombudsperson) ጋር በኢሜይል Ombudsman@seattleschools.org አማካኝነት መወያየት ይችላሉ።

**ለተማሪዎች፣ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ለህዝብ አባላት**፣ስለተጠረጠሩ የአድልዎ ጥያቄዎችን እና ቅሬታዎችን እንዲያስተናግዱ የሚከተሉት ሰራተኞች ተመድበዋል:

- በሕግ ጥበቃ በሚደረግለት ማኅበረሰብ (protected class) ላይ ለተመሰረተ አድልዎ: እባክዎን የተማሪዎች ሲቪል መብቶች ቢሮ (Office of Student Civil Rights) ያነጋግሩ።በስልክ: 206-252-0306. በኢሜይል: OSCR@seattleschools.org. በፖስታ: OSCR, Seattle Public Schools, MS 33-157, P.O. Box 34165, Seattle, WA, 98124-1165.
- ከፆታ መድልዎ ጋር ለተያያዙ ስጋቶች (የፆታ ትንኮሳን ጨምሮ): እባክዎን የ Title IX Coordinator በ Title IX Office በኩል ያነጋግሩ።በስልክ: 206-252-0367. በኢሜይል: Title.IX@seattleschools.org.
- ከአካል ጉዳት መድልዎ ጋር ለተያያዙ ስጋቶች: እባክዎን የ ADA/Section 504 Grievance Coordinator ያነጋግሩ።ስልክ: 206-252-0885.
ኢሜይል: 504Coordinator@seattleschools.org

**ለሰራተኞች** የአካል ጉዳት ነክ ማስተካከያ (accommodations) ጥያቄዎች እና/ወይም የፆታ ትንኮሳን ጨምሮ ከስራ ቅጥር አድልዎ ጋር በተያያዙ የቅሬታ ጉዳዮች፣ እባክዎን የሰው ሃብት ረዳት የበላይ ተመልካችን (Assistant Superintendent of Human Resources) ያነጋግሩ። በስልክ: 206-252-0762. በኢሜይል: HREEOC@seattleschools.org**.** በፖስታ: Assistant Superintendent of HR, Seattle Public Schools, MS 33-157, P.O. Box 34165, Seattle, WA 98124-1166.

**ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች**

**የአድልዎ አቤቱታ አቀራረብ ሂደት**

**ደረጃ 1: ቅሬታ(አቤቱታ) ለትምህርት ዲስትሪቱ ማቅረብ**

በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች፣ቅሬታዎች አድልዎው ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ ባለው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለባቸው። ቅሬታው በጽሁፍ መሆን አለበት፤ ምን እንደተከሰተ በዝርዝር መግለጽ እና አድልዎ (discrimination) ነው ብለው ያመኑበትን ምክንያት ማብራራት ይኖርበታል።ቅሬታዎች በፖስታ፣በኢሜይል ወይም በአካል ለየትኛውም የማዕከላዊ ቢሮ ወይም የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ፣ለተማሪዎች ሲቪል መብቶች ቢሮ (Office of Student Civil Rights) ወይም ለሰው ሃብት (Human Resources) ክፍል ሊቀርቡ ይችላሉ።

የትምህርት ዲስትሪክት የጽሑፍ ቅሬታዎን ሲቀበል፣የዲስትሪክቱን የአድልዎ ቅሬታ ሂደት ቅጂ ይሰጥዎታል።ከዚያም የተማሪዎች ሲቪል መብቶች ወይም የሰው ኃይል ቢሮ  የትምህርት ዲስትሪክቱ ቅሬታውን ለመፍታት እርምጃ መውሰዱን ያረጋግጣል፣ይህም ፈጣን እና ጥልቅ ምርመራን ሊያካትት ይችላል።እንዲሁም ቅሬታዎን ያለ ምርመራ እንደ ሽምግልና ባሉ አማራጭ የግጭት አፈታት ሂደት ለመፍታት ሊስማሙ ይችላሉ።

የትምህርት ዲስትሪክቱ እርስዎ ሌላ ቀን እንዲሆን ካልተስማሙ  ወይም ከቅሬታው ጋር የተያያዙ ልዩ ሁኔታዎች ምክንያት ቀኑን እንዲራዘም ካልጠየቁ በስተቀር፣ቅሬታዎ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ምላሽ መስጠት አለበት።ቅሬታው ከ30 ቀናት በላይ የሚወስድ ከሆነ፣ስለ ማራዘሚያው ምክንያቶች እና ስለሚጠበቀው የምላሽ ቀን በጽሁፍ ይነገርዎታል።

የትምህርት ዲስትሪክቱ ለቅሬታዎ ምላሽ ሲሰጥ፣የሚከተሉትን ማድረጉን ወይም አለማድረጉን በግልጽ ማሳወቅ አለበት:

1. በአቤቱታው ውስጥ የተካተቱትን ክሶች አለመቀበሉን፤ወይም
2. ክሶቹን ማረጋገጥ እና የማስተካከያ እርምጃዎችን መዘርዘር።

በተጨማሪም፣የትምህርት ዲስትሪክቱ ክሱን ካልተቀበለው፣ምላሹ ይግባኝ የማለት መብትዎትን የሚገልጽ ማስታወቂያ እንዲሁም ይግባኙ የት እና ለማን መቅረብ እንዳለበት የሚያሳይ መረጃ ይይዛል።

**ደረጃ 2: ይግባኝ ለበላይ ተመልካች (Superintendent) ማቅረብ**

የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ክሱን ላለመቀበል ባደረገው ውሳኔ ካልተስማሙ፣ለሱፐርኢንቴንደንቱ ይግባኝ ማለት ይችላሉ።የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ለቅሬታዎ ምላሽ ከሰጥዎት(ከተቀበሉ) በኋላ በ 10 ቀናት ውስጥ ለሱፐርኢንቴንደንቱ ቢሮ የይግባኝ ማስታወቂያ በጽሑፍ ማስገባት አለብዎት።

ይግባኙ  በወቅቱ ሲቀርብ፣የበላይ ተመልካቹ (Superintendent) ይግባኙን የሚገመግም ገለልተኛ የጉዳይ ሰሚ መርማሪ (hearing examiner) ይመድባል።ይግባኙ የሚሰማበት ጊዜ የሚቀጠር ሲሆን፣ወደ ችሎቱ ምስክሮችን ወይም ከይግባኝዎ ጋር የተያያዙ ሌሎች መረጃዎችን ይዘው መምጣት ይችላሉ።

ዲስትሪክቱ የይግባኝ ማስታወቂያዎን ከተቀበለ በኋላ በ30 ቀናት ውስጥ የጽሁፍ ውሳኔ ይልክልዎታል።ይህ የጽሁፍ ውሳኔ ለሕዝብ ትምህርት ዋና የበላይ ተመልካች ቢሮ (Office of Superintendent of Public Instruction - OSPI) እንዴት ቅሬታ ማቅረብ እንደሚችሉ የሚገልጽ መረጃ ያካትታል።

**ደረጃ 3: ቅሬታ(አቤቱታ) ለ OSPI ማቅረብ**

በትምህርት ዲስትሪክቱ የይግባኝ ውሳኔ ካልተስማሙ፣ለሕዝብ ትምህርት ዋና የበላይ ተመልካች ቢሮ (Office of Superintendent of Public Instruction - OSPI) ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።ቅሬታው ለሕዝብ ትምህርት ዋና የበላይ ተመልካች ቢሮ (OSPI) መቅረብ ያለበት የዲስትሪክቱን የይግባኝ ውሳኔ በተቀበሉ በ20 ቀናት ውስጥ መሆን አለበት። ቅሬታዎን ለOSPI በሚከተሉት አድራሻዎች መላክ ይችላሉ:በኢሜይል: Equity@k12.wa.us ፤በፋክስ: (360) 664-2967፤ወይም በፖስታ: OSPI Equity and Civil Rights Office, PO Box 47200, Olympia, WA 98504-7200.